የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኢንፎርሜሽንና ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ከሚያዚያ 6 እስከ 13፣ 2017 ዓ.ም
APRIL 14 - 21/2025 G.C

### 1. ቦይንግ የአፍሪካ ቢሮውን በአዲስ አበባ ከፈተ
**ኢዜአ፡ ሚያዝያ 14/2017**

ቦይንግ የአፍሪካ ቢሮውን በአዲስ አበባ ከፍቷል።
ቦይንግ የአፍሪካ ቢሮውን በአዲስ አበባ መክፈቱ ዓለማቀፋዊ ራዕያችንን ለማሳካት ወሳኝ እርምጃ ነው ሲሉ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዓለሙ ስሜ (ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡
ሚኒስትሩ በቢሮው መክፈቻ ስነስርዓት ላይ ተገኝተው ባደረጉትር ንግግር የቢሮው መከፈት በዓለም አቀፉ አቪዬሽን የኢትዮጵያን እድገት ማሳያ ከመሆን ባሻገር የተሳሰረችና የበለፀገች አፍሪካን እውን የማድረግ አለም አቀፋዊ ራዕይን ለማሳካት የሚያግዝ ነው ብለዋል፡፡
ኢትዮጵያ እያደገ የመጣ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አቅም መፍጠሯን የጠቆሙት ሚኒስትሩ በብሔራዊ ትራንስፖርት ካውንስል የሚመራ የዘርፉን መሠረተ-ልማት ለማዘመን፣ የትራንስፖርት ንግድ ወጪን ለመቀነስ እና አፍሪካን ለማስተሳሰር የሚያስችል የአስርት አመታት ፍኖተ ካርታ አዘጋጅተን እየሰራን ነው ብለዋል፡፡
ቦይንግ ቢሮውን በአዲስ አበባ በከፈተበት ሥነ-ስርዓት ላይ የቦይንግ የመካከለኛው ምስራቅ፣ ቱርክ፣ አፍሪካ እና ማዕከላዊ ኤዥያ ፕሬዝዳንት ሚስተር ኩልጅት ጋታ፣ የአሜሪካ አምባሳደር ኤርቪን ማሲንጋ፣ የኢትጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው መንግስቴ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰውና ሌሎችም የኩባንያው አመራሮች መገኘታቸውን ከትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ ያመለክታል፡፡
https://www.ena.et/web/amh/w/amh_6450485

### 2.የኢትዮ-ሳውዲ አረቢያ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ፎረም በሪያድ መካሄድ ጀመረ

**ኢዜአ፤ ሚያዚያ 14/2017**

በፎረሙ ከሁለቱም ሀገራት የተውጣጡ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች፣ የቢዝነስ መሪዎችና የንግዱ ማህበረሰብ ተሳትፈዋል።
በተያያዘም የኢትዮ-ሳዑዲ አረቢያ የጋራ ንግድ ምክር ቤት ስብሰባ በሪያድ ተካሂዷል።
ስብሰባውን በኢትዮጵያ ወገን የንግድ ምክር ቤቱ ሊቀመንበር ሃሰን አብዱላሂ(ዶ/ር) እና በሳዑዲ ወገን የጋራ ምክር ቤቱ ሊቀመንበር አብድላህ አላጃሚ በጋራ መርተውታል።
በውይይቱም ሁለቱ ሀገራት ያላቸውን ታሪካዊ ትብብር በኢኮኖሚው ዘርፍ ማጠናከር እንደሚገባ ተገልጿል።
መድረኩ በሀገራቱ መካከል አዲስ የኢኮኖሚ ትብብር እና የስትራቴጂክ አጋርነት ምዕራፍ እንደሚፈጥር ተነስቷል።
በስብሰባው በንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፍ በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ፣ በግብርና፣ በማዕድን፣ በቱሪዝም እና በኮንስትራክሽን ዘርፎች አብሮ ለመስራት መስማማታቸውን በሪያድ የኢትዮጵያ ኤምባሲ መረጃ ያመለክታል።

**https://www.ena.et/web/amh/w/amh_6446288**

### 3. ለአውሮፓ ህብረት መስፈርት ምላሽ ዝግጁነትን የማጠናከር ጥረት

**Ethiopian press: April 16, 2025**
ለኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት የሚታወቀው ቡና ባለፉት የለውጡ ዓመታት በዘርፉ የተደረጉ ሪፎርሞችን ተከትሎ ይህ ሚናው እየጨመረ መጥቷል:: ወደ ውጪ በሚላክ የቡና መጠንም ከዚህ በሚገኝ የውጭ ምንዛሬም እምርታዎች እየተዘመገቡ ይገኛሉ::
ከኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስሥልጣን የተገኘው መረጃ እንዳመለከተው፤ በ2014 በጀት ዓመት ለውጭ ገበያ ከቀረበው 300 ሺህ ቶን ቡና አንድ ነጥብ 42 ቢሊዮን ዶላር ተገኝቷል ፤ በ2015 በጀት ዓመት ከ240 ሺህ ቶን በላይ ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ አንድ ነጥብ 331 ቢሊዮን ዶላር የተገኘ ሲሆን፣ በ2016 በጀት ዓመትም እንዲሁ ከ298 ሺህ ቶን በላይ ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ አንድ ነጥብ 43 ቢሊዮን ዶላር ማግኘት ተችሏል:: በ2017 በጀት ዓመትም የቡና ምርትና ምርታማነት እያደገ መሆኑን ታሳቢ ያደረገ እቅድ በማዘጋጀት ነው ወደ ሥራ የተገባው:: በበጀት ዓመቱ ወደ 400 ሺህ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ገቢ ለማስገባት ታቅዶ ሲሠራ ቆይቷል::
በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት እንዳሉትም፤ በለውጡ ማግስት 700 ሚሊዮን ገደማ ዶላር በዓመት ከቡና ኤክስፖርት ይገኝ ነበር፤ ባለፈው ዓመት ደግሞ ብዙ እመርታ ተመዝግቦ አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር ተገኝቷል፤ ይህም በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቁ የቡና ኤክስፖርት ተብሎ በወቅቱ ተመዝግቦም ነበር::

https://press.et/?p=149663

### 4. አይ ኤም ኤፍ ለኢትዮጵያ ልማት እና እድገት የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገለጸ

**ኤፍ.ኤም.ሲ ፡ሚያዝያ 14፣ 2017**

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም (አይ ኤም ኤፍ) ለኢትዮጵያ በተለያዩ የልማት ዘርፎች ላይ የሚያደርገውን አጋርነት አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቀ፡፡
የብሔራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምኅረቱ እና የገንዘብ ሚኒስትር አህመድ ሺዴ ከ2025ቱ የዓለም ባንክ ቡድን እና አይ ኤም ኤፍ ስብሰባ ጎን ለጎን ከአይ ኤም ኤፍ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ክሪስታሊና ጆርጂዬቫ ጋር ተወያይተዋል፡፡
ማኔጂንግ ዳይሬክተሯ ወይይቱን ተከትሎ በማኅበራዊ ትስስር ገፃቸው ባሰፈሩት መረጃ÷ ከኢትዮጵያ የፋይናንስ ልዑክ ጋር የምስራቅ አፍሪካ ሀገራትን የኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳዎች በተመለከተ ፍሬያማ ውይይት ማድረጋቸው ገልጸዋል፡፡
በውይይቱ ወቅት አይ ኤም ኤፍ ለኢትዮጵያ ልማት እና እድገት የሚያደርገውን ድጋፍና አጋርነት አጠናክሮ እንደሚቀጥል መግለፃቸውንም አመላክተዋል።
በዋሽንግተን ዲሲ ለስድስት ቀናት በሚካሄደው የ2025ቱ የዓለም ባንክ ቡድን እና አይ ኤም ኤፍ ዓመታዊ ስብሰባ የሁለቱ ተቋማት የጋራ ኮሚቴን ጨምሮ የተለያዩ ሀገራት የፋይናንስ ልዑኮች እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡

https://www.fanamc.com/archives/290735

**5. Ethio-Saudi Arabia Trade, Investment Forum Underway in Riyadh**

**ENA: April 22, 2025**

The Ethio-Saudi Arabia Trade and Investment Forum commenced in Riyadh, Saudi Arabia today.

High ranking government officials and members of the business community of the two countries are taking part at the forum.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_6447725

**6. Opening Up of Previously Closed Sectors Attracting Large Number of Investment to Ethiopia**

**ENA: April 21, 2025**

Ethiopian Investment Commission Commissioner Zeleke Temesgen highlighted that Ethiopia has been undergoing a substantial reform process over the past seven years, achieving commendable results.

The Commissioner stated that during these reform years, sectors previously closed to foreign investors have been opened.

He further noted that the economic reform has brought about improvements capable of bolstering investment.

Commissioner Zeleke pointed to the measures taken in revising the investment law, emphasizing that these steps have unlocked sectors that were previously off-limits to foreign investors.

He mentioned that the Ethiopian Investment Board has permitted foreign companies to engage in wholesale, retail, import, and export trade activities.

The government's decision to open investment sectors that had been closed to foreign companies for extended periods, such as Ethio Telecom and the Special Economic Zone Proclamation, is supporting investment and attracting a large number of foreign investors, he elaborated.

The Commissioner indicated that the Investment Commission has demonstrated strong performance over the past nine months, citing the attraction of foreign direct investment (FDI) which has shown a 2.4 percent growth compared to the previous year.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_6442955

**7. Tariffs Threaten Ethiopian Cut Flower Exports in Thriving US Market**

**The reporter: April 19, 2025**

PM says tariffs may 'open door for more investment'

Flower exporters say the impacts of the Trump administration's tariffs are beginning to make themselves felt, jeopardizing a US market they have been working hard to penetrate over the past few years.

Miserach Berhanu, head of the Ethiopian Flower, Vegetable, Fruit, and Herbs Exporters Association, told *The Reporter* the 10 percent tariff levied on Ethiopia is creating serious challenges for fresh cut flower exporters.

The new tariff adds to an existing three percent duty on flowers in the US, and the sharp increase is expected to slow the progress exporters have made in the US market over the last four years.

https://www.thereporterethiopia.com/44708/

**8. Ethiopia's effort to export value added coffee should be intensified**

Ethiopian coffee, which has achieved historical success in terms of production, quality and revenue, is increasingly in demand in the domestic and international markets. It is stimulating the country's export trade. In particular, its competitiveness and demand at the international level have increased significantly more than ever before.

The reform carried out in the sector has played a major role in the significant changes that have occurred in the coffee sector. Many indicators show that this reform work carried out in the coffee sector over the past five years is achieving encouraging results. One of the main achievements is increasing production and productivity; from the 833 thousand tons of coffee production capacity in the last fiscal year, it has been possible to create a capacity to produce 1.1 million tons of coffee, according to the Ethiopian Coffee and Tea Authority.

In terms of coffee export revenue, it was also between 700 and 800 million Dollars; since the reform efforts, this figure has climbed to a record level of over 1.4 billion Dollars. This figure is expected to reach two billion this year. Many projects are underway to double this income and earn between 2 and 4 billion Dollars from the export trade of raw coffee alone in the coming years.

From the previous situation of exporting less than 300,000 tons per year, more than that amount has been exported in recent years; this year, data indicates that efforts are being made to increase this figure to 450,000 to 500,000 tons.

https://press.et/herald/?p=113932